# ኢህአዴግና የገጠሩ ሕዝብ በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ዙሪያ ይሰራሉ፤ ተቃዋሚዎችና የከተማው ሕዝብ በሊዝ ዙሪያ ይነታረካሉ

(ከአብዱራህማን አህመዲን - የቀድሞ የኢዴፓ አመራር አባል)

**(ይህ ጽሁፍ ረቡዕ የካቲት 14 ቀን 2004 ዓ.ም በታተመው ሰንደቅ ጋዜጣ 7ኛ ዓመት፣ ቁጥር 337 ላይ ቀርቧል። በኢንተርኔት ላይ እንዲታተም ቢረደግ ጋዜጣውን ላላገኙ ሰዎች ግንዛቤ ይጠቅማል በሚል መንፈስ ለአይጋ ፎረም ልኬዋለሁ። መልካም ንባብ)**

ከሁለት ሳምንት በፊት አንድ ዘመዴ ከሀገሪቱ ሰሜናዊ አካባቢ ከአንዲት የገጠር መንደር መጥተው ስለአካባቢያቸው ሁኔታ ተጨዋወትን። ስለ ዘመድ አዝማዱ፣ ስለ አዝመራው፣ ስለ ከብቱ፣ ስለቀየው፣... ጠየቅኳቸው። መንግስትንም "ጥቂት" አማን። የገጠሩ ሕዝብ ሜዳ ተራራውን በመቆፈርና ክትር በመስራት መጠመዱን እኚህ ዘመዴ ነገሩኝ። ለዚህም ሥራ ሕፃን አዋቂ፣ ሴት ወንድ ሳይል ማለዳ ተነስቶ እስከ ቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ እንደሚሰራ እንዲህ በማለት አጫወቱኝ።

"... የኛን ነገር አታንሳው! እቤት የሚውል፣ ቀዬ የሚጠብቅ ጠፍቷል። አቅም ያላቸው ይቆፍራሉ፣ ድንጋይ ያግዛሉ፣ አፈር እንዳይከላ ክትር ይሰራሉ። አቅመ ደካማ ሽማግሌና አሮጊቶች በእግር አዝግመው፣ በፈረስና በበቅሎ ገስግሰው እዚያው ልማቱ የሚሰራበት ቦታ ድረስ ይሄዳሉ...." አሉኝ። "የሚሰሩትስ እሺ። አሮጊትና ሽማግሌዎች ደግሞ ምን ያደርጋሉ?" አልኳቸው - በንግግራቸው መሀል ጣልቃ ገብቼ። "መጀመሪያ ላይ ለኛም ግር ብሎን ነበር። የገባን ኋላ ነው። አሮጊቶች በቁፋሮ የተሰማሩትን ሰዎች ማቲዎች (ሕፃናት ማለታቸው ነው) አንድ ላይ ሰብስበው ያጫውታሉ። ይጠብቃሉ። ምግብና ውሃ ያቀርባሉ። ሲደክማቸው ያስተኛሉ። ሽማግሌዎች ከብቱን፣ ፍየሉን፣ በጉን፣... አንድ ላይ አድርገው ይጠብቃሉ። ይሄ ብቻ አይምሰልህ!... ጎበዛዝቱ አካፋና ዶማውን ይዞ ሲሄድ፣ አንጥረኞች ወናፍና ከሰል ይዘው ይከተላሉ...." አሉኝ። አሁንም አቋረጥኳቸውና "እነሱ ደግሞ ምን ሊያደርጉ?..." በማለት ጠየቅኩ። "በቁፋሮው ሂደት የሚበላሹ ዶማዎችን፣ ማረሻዎችን፣ መጥረቢያዎችንና ማጭዶችን፣... እዚያው ስራው ቦታ ላይ በመጠገን የልማቱን ስራ ለማሳለጥ ነዋ!" አሉኝ። ሙያ ያለው በሙያው፣ ጉልበት ያለው በጉልበቱ ልማታዊ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ መሆኑ ነው።

ጨዋታችንን በመቀጠል "እና... በዚህ ሁኔታ ምን ምን ሰራችሁ?" አልኳቸው - የስራውን መጠን ለማወቅ። "ምን ያልሰራነው ነገር አለ!" አሉኝ ጋቢያቸውን እያጣፉ። በአካባቢው የማውቃቸውን ለዘመናት ተራቁተው እርቃናቸውን የተገተሩ ተራሮችን፣ ሸንተረሮችን፣ አምባዎችን፣ ወንዝና ሜዳዎችን፣... በስም እየጠሩ የአፈር እቀባና የእርከን ስራ መሰራቱን አስረዱኝ። በተከናወነው ስራ እየተገረምኩ፣ በዚህ ሁሉ የስራ ሂደት የሕዝቡ የስራ መንፈስና ስሜት ምን እንደሚመስል ለጥቄ ጠየቅኳቸው።

"የሕዝቡ እንኳ ስሜት የተዘበራረቀ ነው።... የመንግስት አሳብ የገባቸው የገባቸው ከመጣን አይቀር፣ ጊዜ ካባከን አይቀር... በማለት ያለ ምንም መለገም በርትተው ሲሰሩና ሲያሰሩ ቆዬ። አንዳንዶች እያለመጡም እየበረቱም፣ ወለም ዘለም እያሉም እንዲሁ ሲሰሩ ቆዬ። አንዳንዶች ደግሞ በመንግስት የመጣ ትዛዝ በመሆኑ እዚያው እየተገኙ እየተማረሩም፣ በየጥላው አረፍም እያሉ ሲሰሩ ቆዬ... ብቻ ዓይነቱ ብዙ ነው" የሚል ምላሽ ሰጡኝ። መንግስት የአካባቢው ልማት እንዲሰራ ያደረገበት ምክንያት ገብቷቸው እንደሆነ ስጠይቃቸው ደግሞ "ያው የተራቆተውን መሬት በደን ለመሸፈንና አፈሩ እንዳይጠረግ ለማድረግ ነዋ!" አሉኝ። ታዲያ ይህ በመደረጉ የሚጠቀመው ማን ይመስልዎታል?" በማለት ስጠይቃቸው ደግሞ፣ "እሱማ መቼስ እኛው ነንዪ ሌላ ማን ሊሆን! መንግስት ታዲሳባ መጥቶ እዚያ አይኖር፣ አያርስ፣ አይነግድ" የሚል መልስ ሰጡኝ። "ታዲያ ይሄ ምን ያማርራል? ለራሳችሁ ጥቅም መስራቱ ምን ችግር አለው?" የሚል ጥያቄ አቀረብኩና ጨዋታውን አራዘምኩት።

"ነገሩ ዱብ እዳ ሆነብና! ደሞ ሁለት ሳምንት ሦስት ሳምንት የራሳችንን ጉዳይ ትተን፣ እሑድ ሳንል፣ ቅዳሜ ሳንል ድንጋይ ጋር ትግል ሆነኮ!... ፀሐዩም፣ ነፋሱም፣ ቅዝቃዜውም ያማርራል" አሉኝ። "ያካባቢው የመንግስት አካላት ምን እንደምትሰሩ፣ ለምን ያህል ጊዜ እንደምትሰሩና ለምን እንደምትሰሩ፣... ሰብስበው አላማከሯችሁም ማለት ነው?... እዚህ በሬዲዮም በቴሌቪዥንም የሚነገረው ምክክር እንደተደረገና እናንተ አምናችሁበት የስራ ጊዜውን እንደወሰናችሁ ነው" አልኳቸው። "ወይ መመካከር!... ሰው ስብሰባ ሲባል በጄ ብሎ አይወጣ። እኔ ራሴ በስብሰባው ላይ አልተገኘሁም.... ግና አንድ ነገር ሲመጣ ምሬቱ አይቀርም ነው። ጥቂቶች ሰብሰብ ብለው የተነጋገሩ ይመስለኛል... ከዚያ ያለህን መሳሪያ ይዘህ ውጣ ተባልን... ኋላ የሚመጣው ነገር ስለማይታወቅ... ወጣን..." የኔና የዘመዴ ጭውውት በዚህ መልኩ ይቀጥላል።

ይህ ጭውውት ስምንት ዓመት ወደኋላ ወሰደኝ - ወደ 1996 ዓ.ም። የኢዴፓ አመራር በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ሕዝባዊ ስብሰባዎችን በማድረግ በተለያዩ አጀንዳዎች ዙሪያ ከሕዝብ ጋር ምክክር እንዲደረግ ውሳኔ አሳልፎ ነበር። በዚሁ መሰረት ከሌሎች የፓርቲው አመራር አባላት ጋር ወደ ባሌ ጎባ እንድሄድ ተመደብኩ። ከስብሰባው እለት አንድ ቀን አስቀድሞ የአውቶቡስ ጉዞ ጀመርን። ለወትሮው ከአዲስ አበባ ወደ ባሌ በአሰላ በኩል የሚኬድ ቢሆንም፣ መንገዱ በመበላሸቱ ጉዟችንን ያደረግነው በሻሸመኔ በኩል ነበር። ከሻሸመኔ በኋላ ለነበረው አካባቢ አዲስ ስለነበርኩ አጠገቤ ከነበሩ ተጓዥ ጋር ጨዋታ ጀመርኩ።

ሰውየው አካባቢውን እንደሚያውቁት ገልጸውልኝ እያስጎበኙኝ ጉዟችንን ቀጠልን... ኮፈሌ አካባቢ ያለውን ጥቅጥቅ ያለ ደን አሻግሬ እያየሁ በልቤ በማድነቅ ላይ እንዳለሁ "አየኸው ማዶ ያለውን ደን?" ሲሉኝ ጭልጥ ብየ ከገባሁበት የሃሳብ ጫካ መለስ አልኩና "አዎ... የሚገርም ነው" አልኳቸው። "ይህንንስ አየኸው?" አሉኝ፣ ከመኪና መንገዱ ዳር ዳር ተቀርጦ የተከመረውን የባህር ዛፍ አጣና እያመለከቱ። በአዎንታ ራሴን ነቀነቅኩ።

“ይሄ ዛፍ ሲተከል እዚህ ኮፈሌ ተማሪ ነበርኩ። ይሄ ሁሉ ደን የተተከለው በአካባቢው ሕዝብ ነው። በዘመነ ደርግ በስራ ዘመቻ ነው የተተከለው። በወቅቱ የዚህ ወረዳ አስተዳዳሪ የነበረው ሹም የከተማውንም የገጠሩንም ነዋሪ በዱላ እያንቀራጠጠ ነበር ይህንን ሁሉ ከአመስት ኪሎ ሜትር በላይ የሆነ ደን ያስተከለው… ይኸውልህ ይሄኛው መንግስት ደግሞ ድምጹን አጥፍቶ በመጨፍጨፍ ይቸበችባል….” አሉኝ። ረጅም ወሬ ጀመርን። እናም በረጅሙ መንግስትን አማን። ዛፍ ሳይተክል ዛፍ በመቁረጡ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ አድርገን፣ ኩነኔውን አብዝተን ተቸነው። ቆሎውም ጫቱም ጋር አላመጥነው….።

ከዚህ በላይ ያቀረብኳቸው ሁለት ሃሳቦች የዛሬውና የትናንቱ ኢህአዴግ እየሰራቸው ያሉትን ተግባራት የሚያሳዩ ይመስለኛል። “ሕይወት ያለው” ፓርቲ ትናንት የሰራውን በመገምገም፤ ስህተቱን እያረመ፣ ብርታቱን እያጠናከረና እያስፋፋ መሄድ ያለና የነበረ ብቻ ሳይሆን ወደፊትም መሆን የሚገባው ነው የሚል እምነት አለኝ። ወደ ሰሞኑ ሁኔታ ልመለስ…

የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ሰሞኑን በአንድ አጀንዳ ዙሪያ ተደጋጋሚ ዜና እየነገረን ነው። ኢህአዴግ እና የገጠሩ ሕዝብ በመላ ሀገሪቱ በእርከን ስራ፣ በተፈጠሮ ሀብት ጥበቃና የተራቆቱ አካባቢዎችን እንዲያገግሙ በማድረግ ዙሪያ መጠነ ሰፊ የልማት ዘመቻ ስራ በማከናወን ላይ መሆናቸው እየተገለጸ ነው። የኢህአዴግ አባላትና ካድሬዎች ብቻ ሳይሆኑ፤ የፓርቲው ከፍተኛ አመራር አባላትና የመንግስት ባለስልጣናት ጭምር የልማት ዘመቻው በሚከናወንባቸው የገጠር መንደሮች በመገኘት የስራውን ሂደት በቅርበት እየተከታተሉ መሆኑንም ተመልክተናል።

በተቃዋሚውስ ጎራ ምን እየተከናወነ ነው? በተቃዋሚው ጎራ ምን ምን እየተከናወነ እንደሆነ ደግሞ አንዳንድ በግል ይዞታ ስር ያሉ ጋዜጦች እየዘገቡ ነው። አዎ! ተቃዋሚዎችም ቢሆኑ የዋዛ አይምሰሏችሁ! ከምርጫ 2002 ወዲህ ረጅም እረፍት ወስደው እንቅልፋቸውን በመለጠጥ ‘መጠነ ሰፊ ፖለቲካዊ ዝግጅት’ እያደረጉ እንደነበርና ሰሞኑን ደግሞ ኢህአዴግ ያቀበላቸውን “አጀንዳ” አንግበው ‘ንቅናቄ’ ጀምረዋል አሉ። በሊዝ አዋጅ ዙሪያ የከተማውን ሕዝብ ለማወያየት እየተወያዩ ነው አሉ። “ሰሌን አንጥፈው”፣ እቢሯቸው ውስጥ እያደሩና እየዋሉ፣ (አንዳንዶቹ የሃያ ሰዓታት ሪከርድ ሰብረዋል ይባላል) አባላቶቻቸውን ከየክልሉ አሰባስበው እየመከሩ ነው የሚል ዜና ሰምተናል። በቅርብ ቀናት በመስቀል አደባባይ ድልቅልቅ ያለ “ሕዝባዊ ማዕበል” በመፍጠር ኢህአዴግን ፋታ እንደሚነሱት ይጠበቃል¡¡¡

የሀገራችንን ፖለቲካና ፖለቲከኞች ሁኔታ እንዲህ ዳር ላይ ቆመው ሲያዩት እንዴት ይገርማል መሰላችሁ! ኧረ ይደንቃልም! ከዓመታት በፊት በገጠር ያሉ የኢህአዴግ አባላት “አገር አማን” ብለው ተኝተው ሲያንኮራፉ፤ በከተማ ያሉት ደግሞ “በኪራይ ሰብሳቢነት” አባዜ ተጠምደው፣ መሬት በመቸብቸብ ፋታ አጥተው ላይ - ታች ይሉ ነበር። ያኔ ተቃሚዎች በከተማ በብልሹ አሰራርና በሙስና የተጠመዱ የመንግስት አካላትን ለማጋለጥ በየጋዜጣው የመግለጫ ዶፍ ያወርዱ ነበር። አንዳንዶቹ እንዲያውም ማይክሮፎን አንግበው ወደ ክፍለ-ሀገራት በመሄድ የሚያንኮራፉ የኢህአዴግ አባላትን እንቅልፍ ይነሱ ነበር።

ይህም እንቅስቃሴአቸው በምርጫ 97 የተቀዳጁትን የተቃውሞ ድምፅ (Protest Vote) ያስገኘላቸው ይመስለኛል። ዛሬስ?

ዛሬ ዛሬ ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆኗል። ተቃዋሚዎች በምርጫ 2002 ባገኙት ውጤት ተስፋ ቆርጠው፣ በመንቃትና በመተኛት መሀል ላይ ሆነው በቁም ሲያንጎላጁ፣ ኢህአዴግ የሊዝ አዋጅን ድንገት አውጥቶ ያልታሰበ አጀንዳ ሲያቀብላቸው፣ የአጀንዳውን ምንነት በቅጡ ሳያጤኑ፣ በህብረተሰቡ ላይ የሚያስከትለውን ተጽእኖ በእውቀት ላይ ተመስርተው በወጉ ሳይመረምሩ፣ አማራጩን በጽሞና ሳያሰላስሉ፣… የከተሜውን ሕዝብ ስሜት ይነካል በሚል ስሌት (በተለይም አዲስ አበቤውን) “አለንልህ! እኛ እያለን የሊዝ ቀንበር አይጫንብህም!” እያሉ መሆኑን ጋዜጦች እየነገሩን ነው።

የፖለቲካ አጀንዳ የማያልቅበት ኢህአዴግ የሊዝ ፖሊሲን መሰረት ያደረገ “የስኒ ማዕበል” ከቀሰቀሰ በኋላ ወደ ገጠር ወርዶ ለዓመታት ተኝተው የነበሩ አባላቱን፣ ደጋፊዎቹንና የመንግስት አካላትን ያካተተ የሕዝብ ንቅናቄ በመፍጠር ዘላቂነት ያለው (ስትራቴጂክ) ተግባር በማከናወን “ድክመትን የማካካስ” ስራ በመስራት ላይ ይገኛል። ለዚህም ነው ይህንን መጣጥፍ “ኢህአዴግና የገጠሩ ሕዝብ በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ዙሪያ ይሰራሉ፣ ተቃዋሚዎችና የከተማው ሕዝብ በሊዝ ዙሪያ ይነታረካሉ” የሚል ርእስ የሰጠሁት።

ጽሑፌን እፊት ግንድ ከማድረሴ በፊት ጥቂት ነጥቦችን ላክል። በሚመጣው ዓመት በአዲስ አበባ ከተማ የከተማ ምክር ቤቶች ምርጫ የሚካሄድ ይመስለኛል። ከሁለት ዓመታት በኋላ (ሦስተኛው ዓመት የምርጫው ዘመቻ የሚካሄድበት ነው) ሀገራዊ ምርጫ እንደሚካሄድ ይጠበቃል። ለዚሁ ዝግጅት ነው መሰል፣ ተቃዋሚዎች ያንጎላጃሉ… ኢህአዴግ በከተማ “የስኒ ማዕበል” ቀስቅሶ በገጠር ልማታዊ ተግባር ለማከናወን “የሕዝባዊ ማዕበል” ንቅናቄውን ተያይዞታል… የከተሜው “ኪራይ ሰብሳቢ” አዲሱ የሊዝ ፖሊሲ በፈጠረበት ስሜት ግራ ተጋብቷል… ተቃዋሚዎችን ለመደገፍም ሆነ መንግስትን ለመቃወም ድፍረት ያጣ ይመስላል። ውስጥ ውስጡን እያጉተመተመ ዝምታን መርጧል… ገጠሬው ጊዜና ጉልበቱን ከስክሶ በሰራው የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ፣ የአፈር ክትር፣ በድካምና በእርካታ መሀል ሆኖ፣ አካፋና ዶማውን ተደግፎ ጣመኑን ያዳምጣል… የመንግስት ተቋማት “የልማት ሰራዊት” በመፍጠር አገልግሎት አሰጣጣቸውን ለማሻሻል ተግተው ይሰራሉ… ዲያስፖራው እንጃለት!... አልፎ አልፎ ግን በኢንተርኔት ይተጋተጋል፣ በፓልቶክ ይሞሻለቃል…. ፓርላማም ሕግ ያወጣል…. ጋዜጠኛም ያዋጋል ወይም የውጊያውን ገድል ያስተጋባል… ወያላ ይጮኻል…. የኑሮ ውድነት ጣራ ነክቷል….. የኢህአዴግና የተቃዋሚዎች የተቃርኖ መንገዶች ወዴት ያደርሱን ይሆን? በሂደት የምናየው ይሆናል።